# <u>ውጥረትና ስጋት ካልተለየው ክራሞታችን በስተጀርባ</u>

**ሰለሞን ሽፈራው 12-27-17**

ሀገራችን ኢትዮጵያ ከዚያ በፊት እንብዛም ያልተለመደ ዓይነት የሁከትና ብጥብጥ ተግባር ያስተናገደችው፤ በ2008ዓ.ም ታህሳስ ወር ላይ እንደ ነበር አይዘነጋም፡፡ የዚያን ጊዜውን የነውጠኝነት እንቅስቃሴ ያስከተለው ምክንያት ‹‹የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ያዘጋጀው ማስተር ፕላን በመዲናዋ ዙሪያ የሚኖሩ የኦሮሚያ ክልል አርሶ አደሮችን ለከፋ ማህበረ-ኢኮኖሚያዊ ቀውስ የሚዳርግ ነው›› የሚል ቅሬታ ስለነበርም የሁከትና ብጥብጡ ሰለባ የሆኑት በተለይም አንዳንድ የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ዞኖችና ወረዳዎች ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ ለአብነት ያህልም በበርካታ የውጭ ባለሀብቶችም ጭምር ቀዳሚ የኢንቨስትመንት መዳረሻ ተደርገው ከሚመረጡት የሀገራችን ክፍሎች መካከል አንዱ የሆነውን ምዕራብ ሸዋ ዞንን የሁከትና ብጥብጡ ግንባር ቀደም ኢላማ አድርገውት በመስተዋላቸው ምክንያት ስንቱ ለአካባቢው ህዝብ ህልውና ትርጉም ያለው ጠቀሜታ ይሰጣሉ ተብሎ የታመነባቸው የመሰረተ ልማት ተቋማት፤ በቀናት ዕድሜ ውስጥ የመውደም ዕጣ እንደገጠማቸው ማስታወስ ይቻላል፡፡

በተለይም አምቦ ከተማና አካባቢዋን ጨምሮ፤ ከምስራቅ ወለጋ ዞን አንዳንድ የወረዳ ከተማዎች እስከ የምዕራብ አርሲ ዞኗ ሻሸመኔና አካባቢዋ ድረስ ‹‹የአዲስ አበባው ማስተር ፕላን የፊንፊኔ ዙሪያ አርሶ አደሮችን ይጎዳል›› በሚል ቅሬታ ሽፋን የተቀሰቀሰው ሀገር አውዳሚ የተቃዋሚዎች ነውጠኛ ተግባር ሰለባ ሆነዋል፡፡ ድርጊቱ ለኦሮሞ ህዝብ መብትና ጥቅም ተቆርቁረናል የሚሉት ፅንፈኖቹ ቡድኖች፤ ኦሮምኛ ተናጋሪውን ኢትዮጵያዊ ህብረተሰብ ለፈርጀ ብዙ ኪሳራ የዳረጉበት እንደነበርም የሚዘነጋ ጉዳይ አይሆንም፡፡ ከዚያም በኦሮሚያ ስለተፈፀመው የጥፋት ተግባርና ስላስከተለው ማህበረ ኢኮኖሚያዊ ጉዳት ሰምተን ሳናበቃ፤ሌላ ‹‹ከወልቃይት ፀገዴ ህዝብ የማንነት ጥያቄ ጋር የተያያዘ ቅሬታን መነሻ ያደረገና ግን ደግሞ አጠቃላይ ቅኝቱ ተመሳሳይ ሊባል የሚችል ሀገር አውዳሚ የነውጠኝነት አዝማሚያ የተንፀባረቀበት ተቃውሞ በአማራ ክልል ከተሞችም ጭምር ተቀሰቀሰ፡፡

ይልቁንም የሰሜን ጎንደርንና የምዕራብ ጎጃምን ተጎራባች የአማራ ክልላዊ መንግስት ሁለት ዞኖች ባማከለ መልኩ የተስተዋለው እንቅስቃሴ ከኦሮሚያው ክስተት ጋር እጅጉን የሚመሳሰልበት ፀረ ልማት የሃይል እርምጃ የተቀላቀለበት ከመሆኑ የተነሳ ጥቂት የማይባሉ የኢንቨስትመንት ውጤቶችን (ለምሳሌም በባህር ዳር ዙሪያ የነበሩ የአበባ ምርት እርሻዎችን) እንዲሁም ደግሞ ለአካባቢው ህብረተሰብ ተጨባጭ

ጥቅም እንዲሰጡ ሲባል በመንግስት የተገነቡ የማህበራዊ አገልግሎት መስጫ ተቋማትን ከጥቅም ውጭ ያደረገ እንደ ነበር ነው መረጃዎች የሚያመለክቱት፡፡ ያኔ የአማራ ክልልን በአመፅ ተግባር እንቅስቃሴ ለማተራመስ የተሞከረበት የሁከትና ብጥብጥ ክስተት፤ ወደ አዊ ዞንና ወደ ምስራቅ ጎጃም ዞን የመዛመት አዝማሚያ በማሳዬት ላይ እንዳለም፤ 2008ዓ.ም ሊገባደድ ሲል (በክረምቱ ወራት ውስጥ) ጉዳዩ ያሳሰባቸው የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስቴር ክቡር አቶ ሃ/ማርያም ደሳለኝ የሀገር መከላከያ ሰራዊታችን ጣልቃ ገብቶ ሁኔታውን እንዲያረጋጋ ትዕዛዝ ሰጡና ውጥረቱን ማርገብ ተቻለ፡፡

ይሁን እንጂ ብዙም ሳይቆይ መስከረም 22ቀን 2009ዓ.ም የተከበረውን የኢሬቻ በዓል ወዳልተጠበቀ አሳዛኝ ትዕይንት የቀየረው የኦሮሚያ ክልል ሌላ ዙር የሁከትና ብጥብጥ ተግባር ተቀሰቀሰና የነውጠኞቹ ቡድኖች በተጠና ቅንብር ላይ የተመሰረተ ሀገር የማውደም እርምጃ ከመቼውም ጊዜ ይልቅ ተባብሶ ሲቀጥል የተስተዋለበት አሳሳቢ ሁኔታ በመፈጠሩ ምክንያት፤ የኢፌዴሪ መንግስት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ለማውጣት ተገዷል፡፡ እናም ይህቺ ሀገር ከታህሳስ 2008ዓ/ም ወዲህ ሰላሟን ካደፈረሰ፤ እንዲሁም ደግሞ ዜጎቿን ደም ካፋሰስና መሰረተ ልማቷን ካፈረሰ ትርጉም የለሽ አካባቢያዊ ግጭት የፀዳ መረጋጋት ሰፍኖባት የታየችው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ስራ ላይ እየዋለ በቆየባቸው ወራት ብቻ እንደ ሆነ ደፍሮ መናገር ይቻላል፡፡ ዳሩ ምን ዋጋ አለው? የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ተግባራዊ በተደረገባቸው አስር ያህል ወራት የሀገራችን ሰላምና መረጋጋት፤ ከታህሳስ 2009ዓ/ም በፊት ወደ ነበረበት አስተማማኝ ቁመናው የተመለሰ መስሎን እንዳልነበር፤ ገና የአዋጁ መነሳት የተገለፀበት ዜና ከመሰማቱ ግን፤ እዚህም እዚያም የሚከሰቱ ሰው ሰራሽ የፀጥታ መደፍረስ ችግሮችን ማስተናገድ ጀመርን፡፡ እንግዲያውስ እኔ ውጥረትና ስጋት ካልተለየው ክራሞታችን በስተጀርባ የሚል ርእስ በሰጠሁዋት በዚች አጭር ማጣጥፌ ላነሳ የፈለግኩትም የሀገራችን አስተማማኝ ሰላም እንደ ቀልድ እየተናጋ ያለ መስሎ የሚታይበትን እጅግ በጣም አሳሳቢ ወቅታዊ እውነታ ስላስከተለው ትክክለኛ ምክንያት የምር ልንነጋገርባቸው እየተገባ፤ ግን ደግሞ እንብዛም በሚያጠግብ መልኩ ያልተፈተሹ ናቸው የሚል ግምት ባሳደሩብኝ ነጥቦች ዙሪያ የራሴን የግል ምልከታ መሰረት ያደረገ አስተያየት ብሰጥ ለመፍትሔ ፍለጋው ይረዳ ይሆናል ብዬ በማመኔ ነውና አሁን በቀጥታ ወደ ዋናው ጉዳይ አልፋለሁ፡፡

ስለዚህም እንደኔ እንደኔ በቅድሚያ መነሳት ይኖርባቸዋል የምላቸው ቁልፍ ጥያቄዎች ከዚህ ቀጥሎ የተመለከቱት ይሆናሉ፡፡ እነርሱም ደግሞ፤ የኢፌዴሪ መንግስት የሚኒስቴሮች ምክር ቤት ሕገ መንግስታችን ላይ የሰፈረውን የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ የመደንገግ አስፈላጊነት መሠረት አድርጎ፤መስከረም

28ቀን 2009ዓ/ም ያወጣውንና ለአስራ አንድ ወራት ያህል ፀንቶ የቆየውን የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ እንዲያበቃ ማድረግ ነበረብን ወይ? ለዚህ ጥያቄ አዎን የሚል ምላሽ የሚሰጥ አግባብ ያለው ባለድርሻ የመንግስት አካል ካለስ፤ አዋጁ አብቅቷል ከተባለበት ጊዜ ጀምሮ ያገረሸውን ተደጋጋሚና ተመሳሳይ ቅኝት የተላበሰ አካባቢያዊ የፀጥታ መደፍረስ ችግር ያስከተለው ምክንያት ከየት መጣ እንበል? በተለይም ደግሞ የኦሮሚያንና የአማራን ክልላዊ መስተዳደሮች ያማከለ የሰላምና መረጋጋት መጓደል ችግር የሚስተዋልበት አግባብ በደንብ ከተጠና ሰው ሰራሽ ቅንብር የሚመነጭ መፈራረቅን የተከተለ ገፅታ እንዳለው እውን መካድ ይቻላልን? ስለምንስ ነው የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች የምግብ አቅርቦት ጥራት ይሻሻልልን የሚል የተለመደ ቅሬታን መነሻ ያደረገ ተቃውሞ ማሰማታቸው ሳይቀር ብሔራዊ ማንነትን መሠረት ባደረገ መልኩ የተፈጠረ ሀገር አቀፍ የዕርስ በርስ ግጭት እንደሆነ ለማስመሰል ያለመ መጠነ ሰፊ ፕሮፖጋንዳዊ ዘመቻ የተከፈተው? ወዘተ የሚሉ ናቸው፡፡

እንግዲህ የፅሁፌ ማጠንጠኛ የሆነው ሀገራዊ የጋራ ርዕሰ ጉዳይ ስላነሳው መሰረተሃሳብ እውነቱን እንነጋገር ከተባለ፤ ከታህሳስ 2008ዓ/ም ጀምሮ አሁን ላይ ኢትዮጵያ ውስጥ እየተስተዋለ እስካለው የሰላምና መረጋጋት እጦት ድረስ የተከሰቱት የፀጥታ መደፍረስ ችግሮች በሙሉ፤ የሚመሳሰሉበት አንድ ገልህ ገፅታ መኖሩን ለመረዳት የተለየ ዕውቀት አይጠቅም ባይ ነኝ እኔ በግሌ፡፡ ምክንያቱም ደግሞ፤ የፌደራል ስርዓታችንን ያልተማከለ የመንግስታዊ አስተዳደር መዋቅር ገና በቅጡ ያልተደፈኑ ጥቃቅን ክፍተቶች ሁሉ ፤ይበልጥ ሰፍተው እንዲታዩና በሀገራችን ህዝቦች መካከል የብሔር ማንነትን መሰረት ያደረገ የዕርስ በርስ ግጭትና ደም መፋሰስ እያስከተሉ ናቸው ብለን እንድናምን ለማስገደድ ያለመ መሳፍንታዊ የሴራ ፓለቲካ በማውጠንጠን ዕኩይ ተግባር ላይ ከተጠመዱ ዓመታትን ያስቆጠሩት ፅንፈኛ ተቃዋሚ ቡድኖች፤ ይሄን ድብቅ አጀንዳቸውን ለማሳካት ሲሉ የማይፈነቅሉት የክፋትም ሆነ የጥፋት ድንጋይ እንደማይኖር ይታመናልና ነው፡፡ ስለሆነም ጉዳዩን ከዚህ የሀገራችን ፓለቲካ ስር የሰደደ መሰረታዊ ችግር አኳያ ስንመለከተው የሚገለፅልን አንድ መራር እውነታ ቢኖር፤ በተለይም የዛሬዋ ፌደራላዊት፤ ዴሞክራሲያዊት ሪፐብሊክ ኢትዮጵያ የምትከተለውን ህብረ ብሔራዊ የፌደራሊዝም ስርዓት “በአንድ ወይም በሌላ መንገድ ማስወገድ እንደሚገባ” የሚያምኑት የትምክትና የጠባብነት ፓለቲካዊ አስተሳሰብን በማቀንቀን ረገድ የሚታወቁ ፅንፈኞቹ ተቃዋሚ ቡድኖች “የኢህአዴግን ማሊያ ለብሶ የመጫወት ታክቲክ” የሚሉት የሰርጎ ገብነት ፈሊጣቸው ሳይሰራ እንዳልቀረ ነው ማለት ይቻላል፡፡

በግልፅ አነጋገር፤ ከላይ የተጠቆሙትን ሁለት ተቃራኒ ፖለቲካዊ የአስተሳሰብ ፅንፎች ወክለው በድህረ ደርግ ኢትዮጵያ ውስጥ የተከፈተውን አዲስ የታሪክ ምዕራፍ ለመቀልበስ ያለመ የተቃውሞ እንቅስቃሴ ከማድረግ ለአንድም ቀን ጀምበር እንኳን ቦዝነው እንደማያዉቁ ተደጋግሞ የተነገረላቸው አክራሪዎቹ የቀለም አብዮት ናፋቂ ቡድኖች፤ ምናልባትም ከገዢው ፓርቲ የተሻለ ህቡዕ መዋቅር በመፍጠራቸው ባለድርሻ አካላትም ጭምር ለእነርሱ ነውጠኛ አቋም የመወገን አዝማሚያ ይስተዋልባቸው ጀምሯል ማለቴ ነው፡፡ ለዚህ ትዝብት አዘል አስተያየቴ መነሻ ምክንያት ስለሆኑኝ በርካታ ከወቅታዊ የሀገራችን አጠቃላይ እውነታ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ተጨባጭ ማሳያዎች እንደ ምሳሌ ማቅረብ ባያዳግትም ቅሉ፤ አስፈላጊ አይደለም ከሚል እምነት በመነጨ ሆድ ማስፋት አልፈው ዘንድ ወድጃለሁ፡፡ይልቅስ ሀገራችን ኢትዮጵያ ዛሬ ላይ ከምትገኝበት አሳሳቢ የሰላምና መረጋጋት መጓደል ችግር አኳያ ሲታይ የግድ መነሳት ያለበት አንገብጋቢ ጉዳይ ሆኖ የሚሰማኝ ነገር አለ፡፡

እርሱም ኢትዮጵያን በብሔር ብሔረሰብ ህዝቦቿ ጥቃቅን የልዩነት መገለጫ ሰበብ አስባቦች ምክንያት በሚፈጠር አካባቢያዊ የዕርስ በርስ ግጭትና አለመግባባት ለማተራመስ ሲሞክርበት ከሚስተዋለው የፅንፈኞቹ ተቃዋሚ የፓለሪካ ቡድኖች አፍራሽ እንቅስቃሴ በስተጀርባ ያሉት የውጪ ሃይሎች እነማን ናቸው? ለሚለው ጥያቄ የማያወላዳ ወቅታዊ ምላሽ የመፈለግ ጉዳይ ይመስለኛል፡፡ ይሄን ስልም ደግሞ የዛሬዋ ኢትዮጵያን እንደነሶሪያ፤ እንደነ የመንና እንደነሊቢያ ብሎም እንደጎረቤት ደቡብ ሱዳን ህዝቦቿ ጎራ ለይተው ዕርስ በርስ የሚገዳደሉባት የዕልቂት ምድር ለማድረግ ያለመ የብሔር ቅራኔ ላይ የተመሰረተውን የዘረኝነት እሳት ለማቀጣጠል ጥረት እየተደረገበት ያለውን የነውጠኝነት እንቅስቃሴ እጅጉን በተጠና መልኩ የማቀነባበር አሉታዊ ሚና እንደሚጫወቱ ለሚታመንባቸው የእነ ኦ.ነ.ግ እና የእነ ግንቦት ሰባት “የውስጥ አርበኞች” በግፍ ይላክላቸዋል የሚባለውን ገንዘብ የሚረዳቸው የየትኛው ሀገር መንግስት እንደሆነ ይታወቃል ወይ? ማለቴ ነው፡፡

መቸስ አሁንም እንደ ከዚህ ቀደሙ ጣታችንን ሻዕቢያ መራሹ የኤርትራ መንግስት ላይ ብቻ እንቀስር ብንል “ሞኝና ወረቀት የያዘውን አይለቅ!” ከማሰኘት የዘለለ መፍትሔ ሊያስገኝ አይችልም አይደል ወገኞቼ? ስለዚህም ዛሬ እንኳን በፈርጀ ብዙ የህዳሴ ጉዞ ላይ የምትገኝ ሀገር ስለመሆኗ መላው ዓለም አቀፍ ማህበረሰብም ጭምር የመሰከረላትን ኢትዮጵያን በወንድማማች ብሄር ብሔረሰብ ህዝቦቿ የዕርስ በርስ ቅራኔና ግጭት ለማተራመስ ያለመ የጥላቻ ፓለቲካቸውን በማዛመት ተግባር ከተጠመዱት ፅንፈኛ ተቃዋሚ ፓርቲዎች በስተጀርባ ስላሉት የውጭ ሃይሎች ማንነት ሊነገረን ይገባል ለማለት ነው እኔ

የፈለግኩት፡፡ ለአብነት ያህልም ግብፅ ኢትዮጵያ በዓባይ ወንዝ ላይ የምትገባውን ታላቁን የህዳሴ ኤሌክትሪክ ሃይል ማመንጫ ግድብ እንድታቋርጥ ለማድረግ ያለመ ተፅእኖ ለመፍጠር ስትል፤ በብዙ ሚሊዮን ዶላር የሚቆጠር ገንዘብ ሀገራችንን የሚያተራምስ የሁከትና ብጥብጥ ተግባር እያቀነባበሩ የመቀስቀሱን ተግባር ለሚከውኑ ጉዳይ አስፈፃሚዎቿ ስለመመደቧ የሚናገሩ ወገኖች አሉ፡፡

እንደዚህ ዓይነቱን ከታመነ ምንጭ በተገኘ ተጨባጭ መረጃ ተደግፎ ያልቀረበ የህዝብ አስተያየት ሙሉ ለሙሉ አምኖ መቀበል ተገቢ እንደማይሆን ብረዳም፤ ግን ደግሞ ጉዳዩን በቸልታ ማለፍም ተራ የዋህነት መስሎ ነው የሚሰማኝ፡፡ እንዴት ብትሉኝም የዛሬዋን ፌደራላዊት፤ ዴሞክራሲያዊት ሪፐብሊክ ኢትዮጵያ ዜጎች የጋራ ሀገር የሌለን እስኪመስል ድረስ፤ ከእግር ኳስ ፌደሬሽን የአመራር አካላት ምርጫ እስከ የክለባትን ጨዋታ ለመመልከት ስታዲዮም ውስጥ የታደሙ ወጣት ደጋፊዎች፤ አልፎም እስከ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማቶቻችን በዘለቀ ብሔር ተኮር የዕርስ በርስ ውዝግብና ፍጥጫ እንድንጠመድ እያደረገን ካለው “ዕንቀቅልሽ” በስተጀርባ አንዳች ዳጎስ ያለቁሳዊ ጥቅም ያስገኛል ተብሎ የሚገመት የውጭ ሃይሎችን ብርቱ ጉዳይ የማስፈፀም ተልዕኮ ሊኖር እንደሚችል አለመጠርጠር እጅጉን ያዳግታልና ነው፡፡ ለዚህ ለዚህ ከካይሮ አንዳንድ ፓለቲከኞች ፀረ ኢትዮጵያ አቋም የተሻለ ጥርጣሬ ጋባዥ ምክንያት እንደ ሌለም ደግሞ ደፍሮ መናገር ይቻላል፡፡ ለማንኛውም ግን ይህ ጉዳይ የሚመለከታቸው የኢፌዴሪ መንግስት ባለድርሻ አካላት፤ ውጥረትና ስጋት ካልተለየው ሀገራዊ ክራሞታችን በስተጀርባ ስላሉት የውጭ ሃይሎች ትክክለኛ ማንነት፤ በተጨባጭ መረጃ ላይ የተመሰረተ ይፋዊ ማብራሪያ የሚሰጡበት አግባብ ቢኖር ህዝቡ የተሻለ የጥንቃቄ እርምጃ እንዲወስድ ሊረዳ ይችላልና ይታሰብበት እላለሁ፡፡ በተረፈ ለዛሬ እዚህ ላይ ይብቃኝ፡፡ መዓ ሰላማት!